## ለቤተ ክርስቲያን ሕይወት ምለሳ በጣም አስፈላጊ ነገሮች

(ቅዳሜ—የመጀመሪያ የማለዳ ክፍለ ጊዜ)

መልእክት አራት

### ሥልጣን በክርስቶስ አካል ውስጥ እና በአጥቢያ አብያተ ክርስቲያናት ውስጥ

የመጽሐፍ ቅዱስ ንባብ:- ሮሜ 9:23፤ ማቴ. 28:18፤ ኤፌ. 1:22-23፤ ዕብ. 4:16፤ ራእ. 4:2፤ 22:1-2

**I. እግዚአብሔር የመጨረሻው ባለሥልጣን ነው፤ ሥልጣን ሁሉ የእርሱ ነው—ሮሜ 9:21-22:-**

ሀ. የእግዚአብሔር ሥልጣን እግዚአብሔር ራሱ ነው፤ ሥልጣን ከእግዚአብሔር ማንነት ውስጥ ይመጣል—ራእ. 22:1።

ለ. ሥልጣን ሁሉ—መንፈሳዊ፣ ሥፍራዊ እና አገዛዛዊ—ከእግዚአብሔር ይመጣል—2 ቆሮ. 10:8፤ 13:10፤ ዮሐ. 19:10-11፤ ዘፍ. 9:6።

ሐ. ሥልጣንን ማወቅ ከውጫዊ ትምህርት ይልቅ ውስጣዊ መገለጥ ነው—ሐዋ. 22:6-16።

መ. ጌታ ኢየሱስ ከሥልጣን ሥር የነበር ሰው ነበር፤ ራሱን ዝቅ ዝቅ አደረገ፣ የአብን ፈቃድ አደረገ፣ ለሞት፣ ለዚያውም ለመስቀል ሞት እንኳ የታዘዘ ነበር—ማቴ. 8:9፤ ዮሐ. 4:34፤ 6:38፤ ፊልጵ. 2:7-8።

ሠ. በመለኮትነቱ፣ እንደ እግዚአብሔር አንድያ ልጅ፣ ጌታ በሁሉ ላይ ሥልጣን ነበረው፣ በሰብዕናው ግን፣ እንደ የሰው ልጅ እና እንደ የሰማያዊው መንግሥት ንጉሥ፣ በሰማይና በምድር ያለው ሥልጣን ሁሉ የተሰጠው ከትንሣኤው በኋላ ነበር—ማቴ. 28:18።

ረ. አሁን እንደ የምድር ነገሥታት ገዢ፣ በእግዚአብሔር ከፍ የተደረገው ኢየሱስ በሥልጣን ባሉት ሁሉ ላይ ገዢ ነው፤ ለእግዚአብሔር ዘላለማዊ እቅድ መፈጸም በመለኮታዊው አገዛዝ ውስጥ አለቃው ገዢ ነው—ሐዋ. 2:23፣ 36፤ 5:31፤ ራእ. 1:5።

ሰ. በክርስቶስ ዕርገት እግዚአብሔር ክርስቶስን የአካሉ፣ የቤተ ክርስቲያን ልዩና-ብቸኛ ራስ አደረገው፣ እንዲሁም ወደ አጽናፍ-ዓለማዊ ራስነት ሾመው፤ የመላው አጽናፍ-ዓለም ራስ ኢየሱስ ነው—ቆላ. 1:18፤ ሐዋ. 2:36፤ ኤፌ. 1:22-23።

**II. ክርስቶስ ብዙዎች በተካተቱበት መልኩ የአካሉ፣ የቤተ ክርስቲያን ራስ ነው፣ በግል የአማኞች ሁሉ ራስ ነው፤ በእያንዳንዳችን ላይ በቀጥታ ራስ ነው፣ እኛም ሁላችን ከሥልጣኑ ሥር ነን—ቆላ. 1:18፤ 1 ቆሮ. 11:3:-**

ሀ. ክርስቶስ ራስ መሆኑ በአካሉ ውስጥ ያለውን ሥልጣን ሁሉ እርሱ መያዙ ነው—ሮሜ 9:21፣ 23፤ ማቴ. 28:18:-

1. አካሉ በነጻነት መንቀሳቀስ አይችልም፤ መንቀሳቀስ የሚችለው በአካሉ ራስ አቅጣጫ ብቻ ነው።
2. አካሉን እና ብልቶቹን ሁሉ የሚመራው ሥልጣን በአካሉ ራስ ላይ ይመረኮዛል።

ለ. በአካሉ ራስ ሥልጣን ሥር መሆናችን ወይም አለመሆናችን የአካሉን ሕይወት ማወቃችንን ወይም አለማወቃችንን ይወስነዋል—1 ቆሮ. 11:3፤ ኤፌ. 4:15-16፤ ቆላ. 1:18፤ 3:4:-

1. አካሉ ሊኖረው የሚችለው አንድ ራስ ብቻ ነው፣ ሊገዛም የሚችለው ለአንድ ራስ ብቻ ነው—1:18።
2. ክርስቶስ ብቻ ልዩና-ብቸኛው ራስ ነው፣ እኛም በእግዚአብሔር ከፍ የተደረገውን ክርስቶስ ልዩና-ብቸኛ ራስነት በማክበር እና ለዚያ በመመስከር ለእርሱ መገዛት አለብን—ኤፌ. 1:22-23፤ ማቴ 23:8-12።

ሐ. በአካሉ ውስጥ ለመኖር በአካሉ ውስጥ ላለው ሥልጣን እውቅና መስጠት አለብን—ኤፌ. 1:22-23፤ ቆላ. 1:18፤ 2:19:-

1. በአካሉ ውስጥ ያለውን ሥልጣን በተመለከተ ከሁሉ ነገር በፊት በአካሉ ውስጥ ያለው ራስ የሆነው የእርሱ ሥልጣን በመላው አካሉ መፍሰስ ማስፈለጉ ነው—ኤፌ. 5:23-24:-
   ሀ. ለአካሉ ራስ በቀጥታ ስንገዛ ለአካሉም ጭምር እንጠነቀቃለን፤ ለአካሉ ሳንጠነቀቅ ራስ ለሆነው ለእርሱ ሥልጣን እየተገዛን ነው ልንል አንችልም።
   ለ. ጌታ ብቻ የእኛ ራስ ነው፣ እንዲሁም እርሱ ብቻ የገዛ አካሉን ብልቶች እንቅስቃሴ የመምራት ሥልጣን አለው።
2. በአካሉ ውስጥ ሽማግሌዎች እና ሐዋርያት የአካሉን ራስ ሥልጣን የሚያከናውኑ ወኪል ሥልጣኖች ናቸው—ሐዋ. 14:23፤ 1 ጢሞ. 5:17፤ 1 ቆሮ. 12:28:-
   ሀ. በአንድ በኩል የአካሉ ብልቶች በሙሉ በቀጥታ ለአካሉ ራስ ይገዛሉ—ኤፌ. 5:24።
   ለ. በሌላ በኩል ብልቶቹ ለአካሉ ራስ ወኪሎች ይገዛሉ—ዕብ. 13:17።

**III. በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ያለው ሥርዓት በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ካለው ሥልጣን—ልዩና-ብቸኛ የሆነውን የክርስቶስን ራስነት ከማክበር—ይመነጫል—ቆላ. 1፡18፤ ፊልጵ. 1፡1፦**

ሀ. በቤተ ክርስቲያን ውስጥ የሰው አደረጃጀት የለም፣ ነገር ግን መንፈሳዊ ሥርዓት አለ—ቁ. 1፤ 1 ቆሮ. 14፡40፤ 11፡34።

ለ. የቤተ ክርስቲያን ራስ ጌታ የሆነው ክርስቶስ ነው፣ በቤተ ክርስቲያን ያለው ሥልጣን ደግሞ የክርስቶስ ራስነት ነው—ማቴ. 28፡18፤ ቆላ. 1፡18።

ሐ. በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ሥርዓት መኖር አለበት፣ ነገር ግን ይህ ሥርዓት የሚመጣው ከክርስቶስ ራስነት ነው—ኤፌ. 1፡22-23።

መ. እውነተኛ የሆነው የቤተ ክርስቲያን ሕይወት ልምምድ ሊኖረን የሚችለው ልዩና-ብቸኛ ለሆነው የክርስቶስ ራስነት በመገዛት ነው—ቆላ. 1፡18፤ 2፡19፦

1. በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ያለው ሥርዓት የሚመጣው እኛ የክርስቶስን ራስነት ተግባራዊ በሆነ መንገድ በመገንዘባችን ነው—1 ቆሮ. 11፡3፣16፤ ኤፌ. 1፡22።
2. በቤተ ክርስቲያን ውስጥ የክርስቶስን ራስነት ተግባራዊ በሆነ መንገድ ከመገንዘብ የሚመጣው መንፈሳዊ ሥርዓት ከሌለን፣ እውነተኛውን የቤተ ክርስቲያን ሕይወት በተግባር የምንለማመድበት ምንም አይነት መንገድ ሊኖረን አይችልም—1 ቆሮ. 11፡3፤ 14፡40።

**IV. በቤተ ክርስቲያን ውስጥ የእግዚአብሔር ሥልጣን የሚገለጠው እና የሚወከለው በሐዋርያት እና በሽማግሌዎች ነው—12፡28፤ 1 ጴጥ. 5፡1-3፦**

ሀ. እግዚአብሔር ሽማግሌዎችን እና ሐዋርያትን በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ባለሥልጣን እንዲሆኑ ሾሟል—1 ቆሮ. 12፡28፤ ሐዋ. 14፡23።

ለ. ሐዋርያትና ሽማግሌዎች በራሳቸው ሥልጣን የላቸውም፤ ሥልጣን የሚኖራቸው በአካሉ ራስ ሥልጣን ሥር ሲቆሙ ብቻ ነው፤ የአካሉን ራስ ሥልጣን በመወከል በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ሥልጣንን ያንቀሳቅሳሉ።

ሐ. በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ሥልጣኑን ለመግለጥ እግዚአብሔር በእያንዳንዱ አጥቢያ ቤተ ክርስቲያን ሥልጣኑን እንዲወክሉ ሽማግሌዎችን ይሾማል—ቁ. 23፤ ቲቶ 1፡5፦

1. በአጽናፍ-ዓለማዊዋ ቤተ ክርስቲያን ውስጥ ለአጥቢያ አብያተ ክርስቲያናት አስተዳደር ሽማግሌዎችን ይሾሙ ዘንድ ለሐዋርያት ሥልጣንን እና መብትን የሚሰጥ የሐዋርያነት ኦፊስ አለ—1 ቆሮ. 12፡28፤ ሐዋ. 14፡23፤ ቲቶ 1፡5።
2. ሽማግሌዎችን በመሾማቸው ውስጥ መንፈስ ቅዱስ ከሐዋርያት ጋር አንድ ነበር፣ ሐዋርያትም ይህን ያደረጉት በመንፈስ ቅዱስ መሪነት ነበር—ሐዋ. 20፡28።
3. የሽማግሌዎች ሥልጣን የእግዚአብሔርን ሥልጣን ለመወከል እና ለመግለጥ ነው—1 ጴጥ. 5፡1-3።
4. እንደ ጳጳሳት የሽማግሌዎች ዋና ኃላፊነት መግዛት ሳይሆን መንጋውን፣ የእግዚአብሔርን ቤተ ክርስቲያን በእረኝነት ለመንከባከብ፣ ሁሉን-አቀፍ በርኅራኄ የተሞላ እንክብካቤ ለመስጠት ነው—ሐዋ. 20፡28።
5. ሽማግሌነትን በተመለከተ መጽሐፍ ቅዱሳዊው መርህ ብዙነት ነው፤ በሽማግሌነት ብዙነት ውስጥ የተዋሰነ መሪ የለም፣ ልዩና-ብቸኛው የክርስቶስ ራስነት እውቅና ይሰጠዋል፣ ይጠበቃል እና ይከበራል—14፡23፤ ቲቶ 1፡5።
6. በቤተ ክርስቲያን ሕይወት ውስጥ ለሚመሩን መታዘዝ እና መገዛት አለብን (ዕብ. 13፡17)፤ እግዚአብሔር ለሾመው ወኪል ሥልጣን መገዛት ካልቻልን ለእግዚአብሔር መገዛት አንችልም።

**V. ዛሬ በቤተ ክርስቲያን ሕይወት ውስጥ መለኮታዊ አገዛዝ አለ፣ ይህም አገዛዝ ከእግዚአብሔርና ከበጉ ዙፋን ይመጣል—ራእ. 22፡1-2፦**

ሀ. በቤተ ክርስቲያን ውስጥ መለኮታዊው ሥልጣን እንደ ሕይወት፣ እንደ የሕይወት አቅርቦት እና ለሁሉ እንደሚሆን ጸጋ እግዚአብሔር ራሱን ወደ ውስጣችን ለማደሉ ነው፤ ለዙፋኑ በመገዛት ብቻ ለሁሉ በሚሆን በሚፈስሰው የእርሱ ጸጋ ምንጭ መካፈል እንችላለን—2 ቆሮ. 13፡14፤ ራእ. 22፡1-2፤ 16።

ለ. በዕብራውያን 4፡16 ያለው የጸጋው ዙፋን በራእይ 4 ያለው የሥልጣን ዙፋን ነው፣ ይህም በራእይ 22፡1-2 "እንደ ብርሌ የሚያንጸባርቀው የሕይወት ውኃ ወንዝ" (ቁ.1) የሚመነጭበት የእግዚአብሔርና የበጉ ዙፋን ይሆናል፦

1. ምንም እንኳን ዙፋኑ የሥልጣን ዙፋን፣ የራስነት ዙፋን ቢሆንም ከዙፋኑ የሕይወት ውኃ ወንዝ ይፈስሳል—ቁ. 1።
2. ዙፋኑ የእግዚአብሔር ዙፋን ብቻ ሳይሆን የእግዚአብሔር እና የበጉ ዙፋን የመሆኑ ሃቅ ትርጉሙ እግዚአብሔር በበጉ እንደ ጸጋ ለድሰታችን እየፈሰሰ መሆኑ ነው፦

ሀ. ሥልጣንን ከጸጋ ወይም ጸጋን ከሥልጣን ፈጽሞ መለየት የለብንም፤ ጸጋና ሥልጣን አንድ ናቸው—ዕብ. 4፥16፤ ራእ. 22፥1።

ለ. ወደዚህ ዙፋን በመጣን ጊዜ ሁሉ የእግዚአብሔር ጸጋ ወደ ውስጣችን የሚፈስ ወንዝ እንደሆነ ይሰማናል—ዕብ. 4፥16፤ ራእ. 22፥1-2።

3. ዛሬ ጌታ ኢየሱስ በሥልጣን ብቻ አይገዛም፤ በቤተ ክርስቲያን ውስጥ፣ በአብያተ ክርስቲያናት መካከል እና በአብያተ ክርስቲያናት ሁሉ ላይ ሕይወቱ እንደ ጸጋ በመፍሰሱ በኩል እየገዛ ነው—4፥2-3፤ 5፥6፤ 7፥9፤ 22፥1-2።

ሐ. የእግዚአብሔር እና የበጉ ዙፋን፣ ሥልጣን የመለኮታዊው አስተዳደር ምንጭ ብቻ አይደለም፤ የመለኮታዊው ኅብረት ምንጭም ጭምር ነው—ቁ. 1-2፡-

1. ሥልጣን እና ኅብረት በአካሉ ውስጥ ያሉ ሁለት መስመሮች ናቸው—1 ቆሮ. 11፥3፤ 12፥12-13፣ 18፤ 1፥9፤ 10፥16-17።

2. ዙፋኑ የሥልጣን ጉዳይ ሲሆን፣ “ጥሩ ብርጭቆ የሚመስል ጥሩ ወርቅ” ተብሎ በአደባባዩ የተመለከተው የሚፈስሰው ወንዝ የኅብረት ጉዳይ ነው—ራእ. 21፥21፡-

ሀ. ዙፋኑ መለኮታዊውን ሥልጣን ይወክላል፣ ከዙፋኑም መለኮታዊውን ኅብረት እንደሰት ዘንድ የሕይወት ውኃ ወንዝ ይፈስሳል—22፥1-2።

ለ. በዚህ ኅብረት ውስጥ መለኮታዊው ሥልጣን አለ፣ ምክንያቱም በእግዚአብሔር ኢኮኖሚ ውስጥ ሥልጣን ሁልጊዜ ከኅብረት ጋር የሚሄድ ነገር ነውና—2 ቆሮ. 10፥8፤ 13፥10፣ 14።

3. አንድን አጥቢያ ቤተ ክርስቲያን በተግባራዊ መንገድ ለመገንባት የእግዚአብሔርና የበጉ ዙፋን እና ከእግዚአብሔርና ከበጉ ዙፋን የሚመነጨው፣ በአደባባዩ ላይ የሚፈስሰው፣ እንደ ብርሌ የሚያንጸባርቀው የሕይወት ውኃ ወንዝ ያስፈልገናል—ራእ. 22፥1-2።

© 2021 Living Stream Ministry